# ለሐዋርያ ዓውደ ሃሳብ ዓምድ ከአንባቢያን የቀረቡ ጥያቄዎች፡

ማስገንዘቢያ፡ እስከ ጥር 30 ቀን 2010 ዓ.ም የሚደርሱንን የጥያቄ መልሶች በቀጣዩ እትም እናስተናግዳለን።

1. የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎቻችን እንዲህ እርስ በርሳቸው በሚጠላለፉበት ወቅት ገዥው መንግስ በራሱ የውስጥ ችግር ድንገት ጥብቅ ችግር ቢያጋጥመውና መቀጠል ባይችል የኢትዮጵያችን ሁኔታ ምን ሊሆን ወይም ሊመስል ይችላል?

2. በ"ድህረ-ህዋ' መገናኛ (ኢንተርኔት) 'የፖለቲካ ቨረንዳ አዳሪ" (political homeless) የሚል አዲስ ሃረግ ብቅ ብሉዋል፡ ግንዛቤው ምን ማለት እንደሆን ማብራራት ይቻላል?

3. መቻችልና መከባበር በተቃዋሚውች መካከል መቶ በመቶ የጠፋው ለምንድን ነው?

4. በሃሳብ የተለየውን ሁሉ እርስ በርሱ ወያኔ ነህ/ነሽ ከተባባለ ለተቃዋሚው ምን ተቃዋሚ ሊተርፈው ነው?

5. ሥልጣን መግራት እንደ አማራጭ ሊታይ ይችላል?

6. የዓለምን የፖለቲካ ትኩረት በምሳብ በሥልጣን ላይ ያለውን መንግሥት በምርጫ ለማሸነፍ እያንዳንዱ ተቃዋሚ እንዴት ሊተባበር ይችላል?

7. አቶ መልስ ዜናዊ በቅርቡ በአዎሮፓ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የአየር ለውጥ ጉባኤ አፍሪካን በተመለከተ ያሳዩት ድክመት ከእሳቸው ዘመነ ግዛት በሁዋላ ለኢትዮጵያ የሚተርፋት እዳ አለ? ካለ፡ ለምን? እንዴት?

8. ምዕራባዊያን የአቶ መልስ ዜናዊን መንግስት ደግፈው መቀጠላቸው ከራሳቸው ዘላቂ ብሄራዊ ጥቅም አኩዋያ ልክ ናቸው ትላላችሁ? እንዴት?

9. አዲሱ የወያኔ/ኢሃአዴግ ከፍተኛው አገር አጥፊ ተግባሩ ተከብሮ የኖረውን የሀገራችን አጥመ ሃብት በኪራይ መልክ በችርቻሮ መቸብቸብ ነው። ለመሆኑ ይህን እጅግ አጠያያቂ ተግባር የሚያካሂደው ለምን ነው? ለምን በአሁኑ ወቅት? ድርጊቱ የሚያስከትለው የአጭርና የረጅም ጊዜ አደጋ ምንድን ነው?

10. ሽብርን በአሸባሪ ሃይል መከላከል ወይም ማሸነፍ ይቻላል? ሽብርና አሸባሪ እንዲጠፉ ብልሃቱ ምን ይሆን?

11. የሃላፊነትና የመሪነት ሚና (ችሎታ) እንዴት ይከሰታል? ሃላፊነትን ወይም መሪነትን ለመቀበልና ለመስጠት ሚዛኑ ምንድን ነው?

12. የኤርትራ ጉዳይና መዘዙ የተባበሩት መንግስታት በኤርትራ ላይ ካሳለፈው የማዕቀባ ውሳኔና ካለው የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ እንዴት ሊተነተን ይችላል?

13. ሀገራዊውና ዓለም አቀፉ አጠቃላይ ሁኔታ ለሚቀጥሉት ወራትና ዓመታት ምን ሊመስል ይችልላ?

14. ስለ ኢትዮጵያና ሕዝብዋ ሲባል ከኢትዮጵያዊያን ምን ይጠበቃ? የየበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ እንዴት ይቻላል?

ማሳሰቢያ፡

1. የመልስ መላኪያው- hawarya.publications@sympatico.ca
2. Unicode ወይም GeezA ይጠቀሙ
3. ከተቻለ ስልክ ቁጥርዎን አብረው ይላኩ - ለመመካከር ይረዳልና
4. የተለየ ሃሳብ፡ አስተያየት ወይም ጥያቄ ካልዎ እባክዎን ይላኩልን።